የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት

የመምህራን የመኖሪያ ቤቶች ድልድልና አስተዳደር መመሪያ

ጥቅምት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ-ኢትዮጲያ

ማውጫ

መግቢያ 3
አንቀጽ ፡ - አጭር ርዕስ 4
አንቀጽ 2 - ትርጉም 4
አንቀጽ 3 - መርህ 4
አንቀጽ 4 -የተፈፃሚነት ወሰን 5
አንቀጽ 5 - የቤቶች አደላደል 5
አንቀጽ 6 - የተጠቃሚነት መስፈርት 5
አንቀጽ 7 - የቤት ድልደላ ማወዳደሪያ መስፈርት 5
7.1. የሥራ ኃላፊነት (15%) 5
7.2. የትምህርት ማዕረግ (30%) 6
7.3. የአገልግሎት ዘመን (25%) ፤ 6
7.4. የቤተሰብ ሁኔታ (15%) 6
7.5. የሥራ አፈፃፀም (Teaching Efficiency) - (5%) 7
7.6. የማሕበረሰብ አገልግሎት ፣ ጥናትና ምርምር ፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር (5%) 7
7.7. የሥራ ሁኔታ (5%) 7
7.8. ሴት እና /ወይም አካል ጉዳተኛነት (5%) 7
አንቀጽ 8 - የመኖሪያ ቤት ድልደላ ኮሚቴ 7
አንቀጽ 9 - የቤት አደላደል 8
አንቀጽ 10 - የመኖሪያ ቤቶች ስለሚለቀቁበት ሁኔታ 10
አንቀጽ 11 -የመኖሪያ ቤት አስተዳደርና አያያዝ 10
አንቀጽ 12 - የቤት አበል ስለማይከፈልበት 11
አንቀጽ 13 - የመኖሪያ ቤት ውል 11
አንቀጽ 14 - የመኖርያ ቤት የሙብራት ፤ የውሃና የስልክ ወጪዎች 11
አንቀጽ 15 - የመኖሪያ ቤት ዕቃ አቅርቦት 12
አንቀጽ 16 - የመኖሪያ ቤት ጥገና 13
አንቀጽ 17 - የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ግዴታ 13
አንቀጽ 18 - የኢንስቲትዩቱ ግዴታ 14
አንቀጽ 19- የመሸጋገሪያ ድንጋጌ 14
አንቀጽ 20 - ቅሬታ አቀራረብ በተመለከተ 14
አንቀጽ 21 - ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 14

መግቢያ

የመኖሪያ ቤት ወይም የቤት አበል የመምህሩን የስራ ፍላጎት ለመጨመርና ፍልሰትንም ለመቀነስ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሚጠቀሙበት የማበረታቻ ማዕቀፍ አንዱ አካል እንደሆነ ይታመናል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

- የመኖሪያ ቤት ኪራይ ክፍያ ዕለት ከዕለት መናር ምክንያት በመምህራን ላይ እየደረሰ ያለውን የኢኮኖሚ ጫና መቀነስ ብሎም መቅረፍ አሰፈላጊ በመሆኑ፤
- የማስተማርና የምርምር ሥራ የአእምሮ ስራ በመሆኑ መምህራን በተቻለ መጠን ሙሉ ሃሳባቸውን ሥራቸው ላይ እንዲያውሉ ለማስቻልና የተሻለ የሥራ አካባቢ መፍጠር በማስፈለጉ፤
- መምህራን በጥሩ የሥራ ተነሳሽነት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ማድረግ የተቋሙን አላማ ለማሳካት አጋዥ በመሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ለሁሉም ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችለው እና ለመምህራን የሚቀርበውን ጥቅም በእኩልነትና ፍትሐዊነት እንዲጠቀሙ ተገቢውን ለማድረግ፤
- ተቋሙ ያስቀመጠውን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት ከሌላ አካባቢ የሚገኙ መምህራንን ለመሳብ እንዲሁም በማሰተማር ላይ ያሉትን የተቋሙን መምህራንን ረዘም ላለ ጊዜ ለማቆየት የሚያስችል በመሆኑ፤
- በኢንስቲትዩቱ በተለያየ ኃላፊነት ቦታ ላይ አገልግለው ወደ መደበኛ ሥራቸው/የማስተማር/የሪሰርች ሥራቸው የተመለሱ የአካዳሚክ ባለሙያዎች የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄ ሲያቀርቡ በኃላፊነት ያገለገሉበት ግምት ውስጥ እንዲገባ ሌሎችም በአፈፃፀም ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታት እንዲቻል አሰራር ወጥ፣ ፍትሐዊና ግልፅ ለማድረግ፤
- የተቋሙ ንብረት የሆኑትን ተቋሙ ለሚያከፋፍላቸው የመኖሪያ ቤቶች ክፍፍሉ የሚመራበትን ስርዓት ማበጀት አስፈላጊ በመሆኑ እና ፍትሃዊ፣ ግልፅ እና ቀልጣፋ በሆነ ስርዓት ማስተዳደር በማስፈለጉ፤

ተቋሙ ከላይ በተዘረዘሩት ምክኒያቶች የመኖሪያ ቤቶችን ለመምህራን ለማዳረስ ተገቢውን የቤቶች ግንባታ እያካሄደ ሲሆን ይህንን ጥረት አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን ይህንን ዓላማ ለማሳካት አንዱ የሆነውን የቤት ድልደላ መመሪያ በማዘጋጀት በስራ ላይ እንዲውል በማስፈለጉ የተቋሙ የስራ አመራር ቦርድ ይህንን ባለ ሀያ (20) አንቀፅ የቤት ድልደላ መመሪያ በአስራ አራት (14) ገፆች መመሪያ አውጥቷል፡፡

አንቀጽ 1 - አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመምህራን የቤቶች ድልድል መመሪያ 2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አንቀጽ 2 - ትርጉም

2.1. ተቋም ወይም ኢንስቲትዩት ማለት የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ኢንስቲትዩት ነው፡፡

2.2 ቤት ማለት በኢንስቲትዩቱ ባለቤትነት ወይም ተቋሙ የሚያስተዳድራቸውን መኖሪያ ቤቶችን በሙሉ ያካትታል፡፡

2.3 የበላይ አመራር ማለት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ናቸው፡፡

2.4 የመካከለኛ አመራር ማለት በኢንስቲትዩቱ የሚገኙ ዲኖች ፤ የአካዳሚክ ዳይሬክተሮች ናቸው ፡፡

2.5 አካዳሚክ ስታፍ ማለት በማስተማር፣ በጥናትና ምርምር ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በማህበረሰብ አገልግሎት ደረጃ የተቀጠረ መምህር ማለት ነው፡፡

2.6 «አገልግሎት» ማለት አንድ መምህር በተቋሙ የሰጠው አገልግሎት፣ ደመወዝ እያገኘ በትምህርት ላይ የቆየበት እና በዝውውር ወይንም በቅጥር የመጣ ከሆነ ከመዛወሩ ወይንም ከመቀጠሩ በፊት የሰራበት የአካዳሚክ ወይንም የምርምር ተቋም የተሰጠ የአገልግሎት ጊዜ ነው፡፡

2.7 «ነዋሪ» ማለት በተቋሙ የመኖሪያ ቤት ተስጥቶት የሚኖር መምህርን እና ቤተሰቦቹን ማለት ነው፡፡

2.8 «የወል /የጋራ/ መገልገያ» ማለት ሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ መምህራን ሊሚጠቀሙበት የሚችል የጋራ የሆነ የውሃ፣ የሙብራት፣ የልብስ ማጠቢያ ገንዳ እና የመሳሰሉት ማለት ነው፡፡

2.9 «አስተዳደራዊ ውሳኔ» ማለት በመኖሪያ ቤት ድልድል ኮሚቴ ወይም በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተጣርተው በቀረቡ ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው የጽሑፍ ውሳኔ ነው፡፡

2.10 «የድልድል ኮሚቴ» ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የመኖሪያ ቤት ድልድል የሚሰራና ተጠሪነቱ ለቤቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሆነ ጊዚያው ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

2.11 «የማህበረሰብ አገልግሎት» ማለት የአገለግሎት ዘርፍ ባህሪያት ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ መምህር በሙያውም ሆነ ከሙያው ውጭ በተቋሙ ውስጥም ሆነ ውጭ ከማህበረሰቡ ጋር በመቀናጀት በተለያየ የነጻ አገልግሎት ለማህበረሰቡ ችግር ፈች የሆኑ ሀሳቦችን፣ ቴክኖሎጂዎችን እና የመሳሰሉትን በማቅረብ ወደ ተግባር መቀየር እና ውጤት ማስመዝገብ ማለት ነው፡፡

2.12 "የአካል ጉዳተኛ" ማለት 'በደረሰበት የአካል፣ የአእምሮ ወይንም የስሜት ህዋሳት ጉዳት ተከትሎ የሚመጣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ወይንም ባህላዊ መድሎ ሳቢያ በስራ ስምሪት እኩል ተጠቃሚ ያልሆነ ሰው ነው በሚል በአካል ጉዳተኞች የስራ ስምሪት አዋጅ 568/98 የተገለጸውን ያካትታል፡፡

2.13 ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል::

አንቀጽ 3 - መርህ

3.1 የቤቶች ድልድል ኢንስቲትዩቱ የቆመለትን ዓላማ ማሳካት እንዲያስችል የተጠቃሚውን ኃላፊነትና ፍላጎት የአገልግሎት ዘመን እና ሌሎች በመመሪያው የተጠቀሱ መስፈርቶች ግምት ውስጥ ገብተው በተገቢው ውሳኔ ሰጭ አካል በዚህ መመሪያ መሰረት ብቻ ማከናወን፡፡

3.2 በዚህ መመሪያ ከተመለከተው ስርዓት ውጭ የኢንስቲትዩቱን መኖሪያ ቤት መስጠት ህጋዊና ተገቢ አሰራር አይሆንም፡፡

አንቀጽ 4 -የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈፃሚነት የሚኖረው ኢንስቲትዩቱ በሚያስተዳድራቸው ቤቶች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 5 - የቤቶች አደላደል

5.1 የበላይ አመራሮች በሚመለከተው አካል እንደተሾሙ በያዙት የስራ መደብ ምክንያት በዚህ መመሪያ የተቀመጠው መሰፈርት ሳይመለከታቸው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በቅድሚያ የቤት ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

5.2 ሌሎች መምህራንን በተመለከተ በዚህ መመሪያና ሥነ-ሥርዓት መሰረት በቤት ድልድል ኮሚቴ አማካይነት በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በሚደረግ ድልድል ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

5.3 ከኢንስቲትዩት ጋር በሚደረግ የትብብር ወይም የቅጥር ስምምነት መሰረት ለአጭር ጊዜ (እስከ ስድስት ወር) ለሚመጡ የውጭ ሀገር ባለሙያዎችን በተመለከተ ከኢንስቲትዩቱና ከእንግዶች ፍላጉት አንፃር በዚህ መመሪያ የተመለከተው መስፈርትና የቤት ድልድል ኮሚቴ ውሳኔ ሳይጠበቅ በኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ውሳኔ ቤት ሊሰጥ ይችላል፡፡

አንቀጽ 6 - የተጠቃሚነት መስፈርት

6.1 ቤት የማግኘት መብት ተጠቃሚ የሚሆኑት በአካዳሚ ባለሙያነት የተቀጠሩ መምህራንና የአካዳሚክ ሃላፊዎች ብቻ ናቸው፡፡

6.1.1 የአካዳሚክ ሃላፊዎች፣ ዲኖች፣ ዳይሬክተሮች፣ የትምህርት ክፍል ሃላፊዎች ናቸው፡፡

6.1.2 ፕሮፌሰሮች፣ ተባባሪ ፕሮፌሰሮች፣ ረዳት ፕሮፌሰሮች፣ ሌክቸረሮች፤ ረዳት ሌክቸረሮች እና ረዳት ምሩቃን ፣ ለጥናትና ምርምር ፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር እና ለማህበረሰብ አገልግሎት ተብለው የተቀጠሩት ናቸው፡፡

አንቀጽ 7 - የቤት ድልደላ ማወዳደሪያ መስፈርት

የበላይ አመራሮች በአንቀጽ 5.1 መሰረት ከሚስተናገዱት በስተቀር ሌሎች የእድሉ ተጠቃሚዎች ማመልከቻቸው ለድልድል ኮሚቴ ቀርቦ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሰረት በሚያገኙት ውጤት መሰረት ይስተናግዳሉ፡፡

7.1. የሥራ ኃላፊነት (15%)

የኃላፊነት አገልግሎት ማለት አንድ መምህር በተቋሙ ብቻ በከፍተኛ ፣ መካከለኛ እና በታችኛው የአመራር የስልጣን እርከኖች ላይ በበላይነት ሲመራ /ሲያስተባብር/ ለቆየበት ጊዚያት የሚሰጥ ነጥብ ሲሆን አሰጣጡም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- የአካዳሚክ ኃላፊዎች ማለትም:- ዲኖች ፣ የአካዳሚክስ ዳይሬክቶሮቶች ፣ የተከታታይ ትምህርት ዳይሬክቶሬት ፣ ዋና ሬጅስትራር ፣ የተማሪዎች ዲን ፣ 15%
- ምክትል ዲን ፣ ምክትል የአካዳሚክስ ዳይሬክቶሮቶች ፣ የትምህርት ክፍል ሃላፊ ፣ ካይዘን አስተባባሪ፣ ማህበረሰብ አገልግሎት አስተባባሪ ፣ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም አስተባባሪ ወይም በዚህ ደረጃ የሆነ የስራ ኃላፊነት (10%)
- በተቋሙ የመተዳደሪያ ደንብ (Legislation) የተቀመጠውን የአገልግሎት ቆይታ በሙሉ በኃላፊነት አገልግሎት የሰጠ አንድ መምህር ከላይ በትይዩ የተገለጸውን ሙሉ ነጥብ የሚያገኝ ሲሆን ከዚያ በታች ላገለገሉ በዚሁ ስሌት መሰረት ይሆናል፡፡

$$\frac{\text{ያገለገለበት ወራት}}{\text{በመተዳደሪያ ደንቡ (Legislation) የተቀመጠው ከፍተኛ የአገልግሎት ቆይታ ወራት መጠን}} \times \text{የተቀመጠው ትይዩ ከፍተኛ ነጥብ}$$

- በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች ላይ ሲያገለግል የቆየ መምህር የአገልግሎቶቹን አጠቃላይ ድምር ውጤት እስከ ከፍተኛው 15 /አስራ አምስት/ ነጥብ ድረስ ይያዝለታል፡፡

7.2. የትምህርት ማዕረግ (30%)

1. ከተመራማሪ መምህራን ውጭ ያሉ አካዳሚክ ሠራተኞች የትምህርት ነጥብ አሰጣጥ በሚከተለው መልኩ ይሆናል፡፡
    1. ፕሮፌሰር (30%)
    2. ተባባሪ ፕሮፌሰር (27%)
    3. ረዳት ፕሮፌሰር (23%)
    4. ሌክቸረር (19%)
    5. ረዳት ሌክቸረር (15%)
    6. ረዳት ምሩቅ II (11%)
    7. ረዳት ምሩቅ I (7 %)
2. ተመራማሪ መምህር ከላይ በተጠቀሱት ማዕረግ አቻ ግመታ መሰረት ይስተናገዳል፡፡

7.3. የአገልግሎት ዘመን (25%) ፤

1. አንድ መምህር አስር ዓመት ከዚያ በላይ አመት አገልግሎት ካለው ሙሉ ሃያ አምስት (25) ነጥብ የሚሰጥ ሆኖ ከዚያ በታች ላገለገሎ በዚሁ ስሌት ይሆናል፡፡
2. በአንቀፅ ሁለት ንዑስ አንቀፅ ስድስት ስር የተቀመጠው እንዳለ ሆኖ አንድ የአካዳሚክ ስታፍ የቤት አገልግሎት ለመወዳደር በትንሹ ስድስት ወር በተቋሙ ማገልገል አለበት፡፡ ይህም ማለት ወደ ተቋሙ በዝውውር ወይንም በቅጥር ከሌላ ዩኒቨርሲቲ የመጣ ከሆነ ወደ ተቋሙ ከመምጣቱ በፊት በተመሳሳይ ዩኒቨርሲቲ የነበረው አገልግሎት በሙሉ ይያዛል፡፡ ሆኖም አገልግሎቱ የሚያዘው በዚህ ተቋም ውስጥ በዝውውር ወይንም በቅጥር ከመጣ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው ፡፡
3. ወደ ተቋሙ በዝውውር ወይንም በቅጥር የመጣ መምህር ወደ ተቋሙ ከመምጣቱ በፊት በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፣ በኮሌጅ እና በምርምር ማእከላት ወይም በሌሎች ተዛማጅ የስራ መስኮች የሰራ ከሆነ የነበረው አገልግሎት በግማሽ ይያዛል፡፡ ሆኖም አገልግሎቱ የሚያዘው በዚህ ተቋም ውስጥ በዝውውር ወይንም በቅጥር ከመጣ ከስድስት ወር በኋላ ነው፡፡

7.4. የቤተሰብ ሁኔታ (15%)

1. ሁለትና ከሁለት ልጆች በላይ ያለው - 15%
2. አንድ ልጅ ያለው - 12%
3. ልጅ የሌለው - 7%

7.5. የሥራ አፈፃፀም (Teaching Efficiency) - (5%)

7.5.1. የአንድ መምህር ለመወዳደር ካመለከተበት ጊዜ በፊት ያለው የአንድ አመት (የሁለት ተከታታይ ሴሚስተሮች) የስራ አፈፀፀሙ ተሰልቶ የሥራ አፈጻጸም 100 /መቶ/ ፐርሰንት ከሆነ ሙሉ 5 /አምስት/ ነጥብ የሚያገኝ ሲሆን ውጤቱ ከዚህ በታች ከሆነ በዚሁ ስሌት የሚሰራ ይሆናል፡፡

7.6. የማሕበረሰብ አገልግሎት ፣ ጥናትና ምርምር ፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር (5%)

የዚህ አንቀፅ ተፈፃሚነት በተቋሙ መተዳደሪያ ደንብ ወይንም ሰኔቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

7.7. የሥራ ሁኔታ (5%)

ሀ. በሥራ ላይ የሚገኝ (On Duty)... 5%

ለ. በሀገር ውስጥ የትምህርት ፈቃድ ላይ ያለ 3%

ሐ. በውጭ ሀገር የትምህርት ፈቃድ ላይ ያለ 2%

7.8. ሴት እና /ወይም አካል ጉዳተኛነት (5%)

1. ለ ሴት እና /ወይም አካል ጉዳተኛነት የሚሰጠው ነጥብ ከጠቅላላው የማወዳደሪያ ነጥቦች ድምር ማለትም ከ 100% ውጭ የሚሰጥ ተጨማሪ ነጥብ ይሆናል፡፡
2. የአካል ጉዳተኞች በህክምና ቦርድ የተረጋገጠላቸው ሆኖ ማየት የተሳናቸው (አይነ ስውር) ወይም መስማት የተሳናቸው ወይም በድጋፍ የሚንቀሳቀስ ከሆነ ያለውድድር የመኖሪያ ቤት እንደ አገልግሎታቸው የሚሰጣቸው(የሚመደቡ) ሆኖ ለሌላ አካል ጉዳተኛ ከዚህ በታች በተመለከተው የነጥብ አሰጣጥ ውስጥ የተመለከተውን ያገኛል፡፡

   ሀ. ፆታ፡ ለሴት 3% ፣

   ለ. አካል ጉዳተኛ (4.5%)

   ለ. ሴት አካል ጉዳተኛ (5%)

7.8 በሁሉም መስፈርቶች ተወዳድረው እኩል ነጥብ ያገኙ ተወዳዳሪዎች ቅድሚያ ለሴት የሚሰጥ ሆኖ ተመሳሳይ ፆታ ከሆነ በእጣ ይለያሉ፡፡

አንቀጽ 8 - የመኖሪያ ቤት ድልደላ ኮሚቴ

ኢንስቲትዩቱ የመኖሪያ ቤት ድልደላ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

8.1 ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለምክትል ዋና አስተዳደር ዳይሬክተር ይሆናል፡፡

8.2 የቤት ድልደላ ኮሚቴ ጊዜያዊ (የአጭር ጊዜ) የመኖሪያ ወይም የማረፊያ ቤት ጥያቄዎችን አይመለከትም፡፡

8.3 ኮሚቴው አምስት አባላት ይኖሩታል፡፡ አባላቱም፡-

1. ሁለት አባላት በዋና ዳይሬክተር ይሰየማሉ፡፡ ከሁለቱ አንዱ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡
2. ሁለት አባላት በመምህራን የሚመረጡ ሲሆን አንድ ወንድ ፣ አንድ ሴት ይሆናሉ፡፡
3. የቤቶች አስተዳደር ቡድን መሪ ፀሐፊ ይሆናል፡፡
4. ኮሚቴው ለሁለት ዓመት የሚያገለግል ሆኖ ይደራጃል፡፡ ሆኖም ግን የኮሚቴው አባላት ለሁለት የአገልግሎት ጊዜ ሊሰየሙ ይችላሉ፡፡

8.4 የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

8.4.1 ኮሚቴው አዲስ የመኖሪያ ቤት ሲኖር ወይም ሲለቀቅ ከቤቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሚቀርብለትን መረጃ መሰረት አድርጎ ፍላጉቱ ያላቸው የአካዳሚክ ባለሙያዎች እንዲወዳደሩ ማስታወቂያ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

8.4.2 ኮሚቴው አዲስ የመኖሪያ ቤት ሲኖር ወይም ሲለቀቅ ከቤቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሚቀርብለትን መረጃ መሰረት በማድረግ (ስለተለቀቀው ቤት እና ስለጠየቁት የአካዳሚክ ባለሙያዎች ማህደር) ከዚህ ቀጥለው የተቀመጡትን የዚህ አንቀፅ ሌሎች ንዑስ አንቀፆች ይተገብራል፡፡

8.4.3 የንብረት እና ጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊ ፣ የቤቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ፣ የመምህራን ተወካይ ያሉበት ንዑስ ኮሚቴ ተወዳዳሪዎችን በመስፈርቱ መሰረት መረጃውን አጠናቅሮ ለኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

8.4.4 ኮሚቴው የቤት ድልደላ ወይም ለውጥ ጥያቄ ያቀረቡ ሰራኞች ዝርዝር ሲቀርብለት የሚያስፈልጉትን ሰነዶች ማለትም፡-

ሀ/ ጥያቄ የቀረበበትን ማመልከቻ ቅጽ

ለ/ የመኖሪያ ቤቱን ማህደር

ሐ/ የተወዳዳሪዎችን የግል ማህደር አስቀርቦ ያያል፡፡

8.4.5 ኮሚቴው ጥያቄውን በሚመረምርበት ጊዜ፡-

ሀ/ ለድልደላ የቀረበውን የቤት ደረጃ /ዓይነት/

ለ/ የቤት ጠያቂወችን ሀላፊነት ደረጃና የቅድሚያ መብት ቅደም ተከተል አንፃር በማገናዘብ

ሐ/ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ ይመለከታል ፡፡

8.4.6 ኮሚቴው የቀረበለትን ጥያቄ በአዘጋጀው መስፈርት መሰረት አወዳድሮና መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል

8.4.7 በውሳኔ አሰጣጥ ላይ በኮሚቴ አባላት መካከል የሃሳብ ልዩነት ሲኖር በድምጥ ብልጫ ውሳኔ የመስጠት አሰራር ተግባራዊ ይሆናል ፡፡ ድምፅ እኩል ሲሆን ሰብሰቢው ያለበት ወገን ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

8.4.8 በዚህ መመሪያ መሰረት ተወዳዳሪ ተጠባባቂ የሆኑ የአካዳሚክ ባለሙያዋች በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የሚለቀቅ ቤት ካለ ያለተጨማሪ ውድድር የተወዳደሩበት ቤት ተመሳሳይ መሆኑ እየተረጋገጠ ቤት ይሰጣቸዋል፡፡

አንቀጽ 9 - የቤት አደላደል

9.1 ክፍት ቤት ሲኖርና በማስታወቂያ ሲገለፅ የቤት ጥያቄ የሚቀርበው ለቤት ጥያቄ ማቅረቢያ የተዘጋጀውን ቅፅ በመሙላትና ከሚሰሩበት ዲፓርትመት ወይም የስራ ክፍል የድጋፍ ደብዳቤ በማያያዝ ለቤቶች አስተዳደር ይሆናል፡፡

9.2 በእንግዳ ማረፊያ ቤት ወይም በመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ለአጭር ጊዜ የሚቆዩ የውጭ አገር እንግዶች ሲመጡ መጀመሪያ በኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊ የተገባ ውል ካለ ብቻ የሚመለከተው የስራ ክፍል ለቤት ጥየቄ ማቅረቢያ የተዘጋጀውን ቅፅ ሞልቶ ከተገባው ውል ጋር አያይዞ አንድ ወር ቀደም ብሎ ለቤቶች አስተዳደር ቡድን ይልካል ፡፡ በተገባው ውል መሰረትም ተሰልቶ ቤት ይሰጣቸዋል ፡፡

9.3 ተቋሙ ካለበት የቤት ችግር አኳያ ቅድሚያ ለኢትዮጵያውያን መምህራን መስጠት ስላለበት ከላይ በተራ ቁጥር 9.2 ከተጠቀሰው ውጭ በመደበኛ ቅጥር ለሚመጡ የውጭ ዜጎች የመኖሪያ ቤት አይሰጥም ፡፡

9.4 የቤቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች እና በክፍትነት የሚገኙ መኖሪያ ቤቶችን ሁኔታ በቅደም ተከትል መዝግቦ ለመኖሪያ ቤት ድልደላ ኮሚቴ ያቀርባል ፡፡

9.5 የቤት ድልደል ኮሚቴ የቤት ድልደላውን በመስፈርቱ መሰረት አከናውኖ የውሳኔ ሃሳብ ተጠሪ ለሆነበት አካል ያቀርባል፤

9.6 ድልድሉ ፀድቆ በደብዳቤ እስኪገለጽ ድረስ ማንኛውም የአካዳሚክ ባለሙያ ወደ ተደለደለበት ቤት መግባት አይችልም ፡፡ በድልድሉ መሰረት ቤት የተሰጣቸው መምህራን በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ያለበቂ ምክኒያት ካልገቡ ቤቱ ለሚቀጥለው ተጠባባቂ ይሰጣል ፡፡

9.7 የተቋሙ መምህራን የሆኑና ቤት የሚገባቸው ባልና ሚስት የቤት አሰጣጥ በንዑስ አንቀጽ 5.1 እና 5.2 እንደተጠቀሰው ሆኖ ባልና ሚስቱ ለመኖሪያ ቤት ውድድር ሲቀርቡ የሚወሰድው ነጥብ ከሁለቱ የአንደኛው ከፍተኛውን ድምር የያዘውን ይሆንና ተጨማሪ አምስት ነጥብ (5%) ይሰጣቸዋል፡፡ ባልና ሚስት መለያየት በሚያጋጥም ጊዜ በሁለቱ ስምምነት ቤቱን በማስተዳደር ጉዳዩ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ስምምነት በማይኖርበት ጊዜ ልጆች ከሌላቸው ሴቷ መምህር በቤቱ የመቆየት መብት ይኖራታል፡፡ ሆኖም ወንዱ መምህር ከባለቤቱ ጋር ፍች መፈፀሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቦ ሌላ ቤት ለማግኘት መወዳደር ይችላል፤ ልጆች ካሏቸው በቤቱ የመቆየት መብት ልጅ ለሚይዘው ይሆንና ሌላኛው ወገን ከባለቤቱ ጋር ፍች መፈፀሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቦ ሌላ ቤት ለማግኘት መወዳደር ይችላል።

9.8 የመኖሪያ ቤት የተሰጠው ማንኛውም መምህር የኢንስቲትዩቱ አስተዳደር ሳይፈቅድለት የተሰጠውን ቤት ለቆ ወደ ሌላ ቤት መዛዋር ወይም መቀየር አየችልም ፡፡ ማለትም በግለሰቦች ፍቃድ ቤት መቀያየር ፈፅሞ የተከለከለ ነው ፡፡

9.9 አንድ መምህር በወድድር ያገኘውን ቤት ካልፈለገው ቤቱ ከሱ ቀጥሎ ለሚገባው ሰራተኛ በተቋሙ በኩል ይሰጣል ፡፡

9.10 ማንኛውም በኢንስቲትዩቱ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖር ሰራተኛ ለሌላ የተሻለ ቤት የመወዳደር መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ሆኖም ይህ የሚሰራው የሚፈልገው ቤት ለውድድር ከቀረበ ብቻ ነው፡፡

9.11 በመኖሪያ ቤት ድልደላ ቅሬታ ያለው ማንኛውም መምህር ቅሬታውን በ7 ቀናት ውስጥ ለቤቶች አስተዳደር ዳይሬክተር ማቅረብ ይኖርበታል ፡፡

9.12 ማንኛውም ቤት የተሰጠው ሰራተኛ ከተቋሙ ጋር የሚገባውን ውል ተፈፃሚ ማድረግ ይኖርበታል ፡፡

9.13 ለአጭር ጊዜ መጥተው በእንግዳ ማረፊያ የሚቆዩ እንግዶችን በተመለከተ ጥያቄው ለአስተዳደርና ዋና ዳይሬክተሩ ከአንድ ወር በፊት እንዲቀርብ ተደርጎ የሚወሰን ይሆናል ፡፡

አንቀጽ 10 - የመኖሪያ ቤቶች ስለሚለቀቁበት ሁኔታ

10.1 ሀ/ መምህራን በዝውውር ፣ በእድገት ወደ ሌላ መስሪያ ቤት ወይም ከአካባቢው በመዛወር ከስራ ገበታቸው የሚለዩ ከሆነ የ3 ወር ጊዜ ተሰጥቷቸው የያዙትን ቤት እንዲለቁ ይደረጋል ፡፡

ለ/ መምህራን በሞት የተለዩ እንደሆነ ቤተሰቦቻቸው እስኪፅናኑና አማራጭ እስኪፈልጉ ድረስ የሁለት አመት ጊዜ ተሰጥቷቸው ቤቱን እነዲለቁ ይደረጋል፡፡

ሐ/ ለትምህርት ሄደው ማይመለሱ ፤ በጡረታ ከስራ የተሰናበቱ ቤቱን እንዲለቁ ይደረጋል ፡፡

መ/ በዲስፕሊን ለተባረሩ ወዲያውኑ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ቤቱን እንዲለቁ ይደረጋል፡፡

ሠ/ መምህራን ቤተሰብ (ሚስት /ባልና ልጆች) ከሌሏቸው ለትምህርት በሚሄዱበት ጊዜ የያዙትን ቤት አስረክበው መሄድ አለባቸው፡፡ ትምህርታቸው በአዲስ አበባ ከሆነ(ለሚሆን) ማስረከብ አይጠበቅባቸውም፡፡

10.2 ለምርምር ወይም ሰቫቲካል ሊቭ የወሰደ ወይም ተቋሙ ለሚፈቅደው ሌላ ስራ ከሰራ ገበታቸው ከአንድ አመት ለማይበልጥ ጊዜ ለሚለዩ የአካዳሚክ ባለሙያዎች የተሰጠው መኖሪያ ቤት በይዞታ ስር እንዳለ ሊቆይ ይችላል ፡፡ ሆኖም መምህሩ በአስራ ሁለት (12) ወር ውስጥ ስራውን ወይም ስልጠናውን ጨርሶ ወደ ስራው ካልተመለሰ የሶስት (3) ወር ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ቤቱን ኢንስቲትዩቱ ይረከባል ፡፡

10.3 ከላይ በ10.1 (ሠ) በተጠቀሰው መሰረት በትምህረት ላይ ያሉና መኖሪያቸውን አስረክበው ወደ ውጭ አገረ የሄዱ መምህራን ትምህረታቸውን አጠናቀው ወደ ስራቸው ሲመለሱ ለውድድር ቤት ሲለቀቅ ያስረከቡት ቤት ተመሳሳይ እንዳመጣጣቸው ቅደም ተከተል የተመለሱበት ጊዜ ታሳቢ ተደርጎ ቤት ይሰጣቸዋል ፡፡

10.4 የበላይ አመራሮች ከሀላፊነት ከኢንስቲትዩቱ በሚነሱበትና በሚቀየሩበት ወቅት፡-

የበላይ አመራሩ የአገልግሎት ጊዜውን አጠናቆ ወይንም በሌላ አሳማኝ ግላዊ ምክንያት ወይም በኢንስቲትዩቱ ስራ አመራር ቦርድ ወሳኔ መሰረት ካለበት የስራ ሀላፊነት ላይ ተነስቶ በኢንስቲትዩቱ የሚያገለግል ከሆነ ለአመራሩ የሚመጥን ቤት እስኪሰጠው ድረስ በጊዚያዊ ማረፊያ ቢቶች እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

አንቀጽ 11 -የመኖሪያ ቤት አስተዳደርና አያያዝ

11.1 በኢንስቲትዩቱ ስር የሚገኙ መኖሪያ ቤቶች አያያዝና አስተዳደር በኢንስቲትዩቱ የቤቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት አማካኝነት ይከናወናል ፡፡

11.2 አንድ መምህር የተሰጠውን ቤት በአግባቡ መያዝና መንከባከብ አለበት ፡፡ ቤቱ ለመኖሪያ ቤትነት ብቻ ለተፈቀደለት ነዋሪ ወይም በዚህ ደንብ ሊወከሉ ለተፈቀደላቸው ሰዎች ብቻ መኖሪያነት ያገለግላል ፡፡

11.3 ከአያያዝ ጉድለት በመኖሪያ ቤቱ ላይ ለሚደርሰው ማንኛውም ጉዳት ወይም ብልሽት ቤት የተሰጠው ግለሰብ ተጠያቂ ነው ፡፡

11.4 መምህሩ በኢንስቲትዩቱ ካልተፈቀደለት በስተቀር ቤቱ ላይ ምንም አይነት ማሻሻያ ወይንም ማናቸውንም ዓይነት ለውጦች ማድረግ አይችልም ፡፡

11.5 መምህሩ በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት በአካባቢው በማይኖርበት ጊዜ ቤቱን እንዲያስተዳድሩለት ወክሎ ለኢንስቲትዩቱ በጽሁፍ የሚያሳውቀው ሰው በቤቱ ኗሪ ለሆነ የአካዳሚክ ባለሙያው ባል /ሚስት ፣ ለአቅመ አዳም ላልደረሱ ልጆች ደግሞ ለህጋዊ ሞግዚት ብቻ ይሆናል ፡፡

11.6 መምህሩ ከተቋሙ በሚለቅበት ጊዜ በቤቱ የሚኖር ቤተሰብ ከሌለውና በንብረት እርክክብ ወቅት በጊዜ እጥረት ምክንያት ቤቱን ማስረከብ ባይችል የመኖሪያ ቤቱን የሚያስረክብለት ዋስ የተቋሙ ቋሚ ሰራተኛ የሆነ መወከል ይችላል ፡፡ ዋሱ በሳምንት ጊዜ ውስጥ ቤቱን መልሶ ማስረከብ አለበት ፡፡ቤቱን በወቅቱ ካላስረከበ ኢንስቲትዩቱ ተገቢውን አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ፡፡

11.7 ማንኛውም ቤት የተሰጠው መምህር በመኖሪያ ቤቶች አያያዝና አስተዳደር በተዘጋጀው ውል ላይ መፈረም አለበት

11.8 የቤቶችን አስተዳደርና አያያዝ የሚከታተልና የሚያግዝ የኗሪዎች ኮሚቴ ይቋቋማል ፡፡ ኮሚቴው የሚተዳደርበት ዝርዝር የመተዳደሪያ ደንብ በመኖሪያ ቤቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ይዘጋጃል፡፡

አንቀጽ 12 - የቤት አበል ስለማይከፈልበት

12.1. በኢንስቲትዩቱ ባለቤትነት በሚገኝ ቤቶች የሚኖሩ መምህራን እና የተቋሙ አመራሮች ለቤት አበል በመንግስት የተቀመጠው ክፍያ አይከፈላቸውም ፡፡ የቤት አበሉ የቤት ኪራዩን ይሸፍናል፡፡

አንቀጽ 13 - የመኖሪያ ቤት ውል

13.1. ከጊዜያዊ ማረፊያ ቤቶች በስተቀር ከኢንስቲትዩቱ ጋር የጽሁፍ ውል ሳይደረግ በኢንስቲትዩት መኖሪያ ቤት መኖር አይቻልም ፡፡

13.2. ከኢንስቲትዩት ጋር የመኖሪያ ቤት ውል ሳይፈጽም ወይም በዚህ ደነብ ውክልና ሊሰጣቸው ከሚችሉት ሰዎች አንዱ ሳይሆኑ ኢንስቲትዩቱ በሚያስተዳድረው ቤት ውስጥ ሲኖር የተገኘውን ማንኛውም ግለሰብ ቤቱን በ48 ሰአት ውስጥ እንዲለቅ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም ለዲሲፒሊን ኮሚቴ ቀርቦ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድበት ይደረጋል፡፡ የኢንስቲትዩቱ ሰራተኛ ካልሆነ በሀገሪቱ ህግ መሰረት የወንጀል ክስ እንዲመሰረትበት ይደረጋል ፡፡

አንቀጽ 14 - የመኖርያ ቤት የመብራት ፤ የውሃና የስልክ ወጪዎች

~~14.1. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዳይሬክተሮችቤት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ የውሃ ፣ የመብራትና የስልክ ወጪ አይከፍሉም ፣ ሆኖም የስልክ አገልግሎት ወርሀዊ ጠቅላላ ወጪው ከብር 1000.00 (አንድ ሺ ብር) ከበለጠ ልዩነቱን በቀጥታ ከደመወዛቸው እየተቀረጠ እንዲከፍሉ ይደረጋል ፡፡~~

ለተሿሚዎች በመንግስት መመሪያ ቁጥር በተፈቀደው መሰረት ተናቦ የሚስተካከል

14.2. በመንግስት ወይም በኢንስቲትዩት ደረጃ በተደረገ ስምምነት ለአጭር ጊዜ የመጡ የውጭ ባለሙያዎች የመብራት እና የውሃ ወጪዎችን አይከፍሉም ፡፡ ሆኖም ጠቅላላ ወጪው ለእያንዳንዱ አገልግሎት በስራ ውል ስምምነታቸው ላይ ከተገለጸው የገንዘብ መጠን ሊበልጥ አይችልም ፤ ከዚያ በላይ ከሆነ ልዩነቱን ከደመወዛቸው፤ ደመወዝ የሌላቸው ከሆነ ከሌላ የሚታወቅ የገቢ ምንጫቸው ላይ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡ ወይም ያመጣቸው የስራ ክፍል ሀላፊነቱን እንዲወስድ ይደረጋል ፡፡

14.3. በኢንስቲትዩት ባለቤትነት በሚተዳደሩ ቤቶች የሚኖሩ መምህራኖች የተጠቀሙበትን የውሀ፣ የመብራትና የስልክ ወጪ ይሸፍናሉ፡፡

አንቀጽ 15 - የመኖሪያ ቤት ዕቃ አቅርቦት

15.1. ኢንስቲትዩት ለዉጭ ዜጎችና ለበላይ አመራሮች ለሚሰጣቸዉ የመኖሪያ ቤቶች አቅም በፈቀደ መጠን የቤት ዉስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ያድላል፡፡ ለኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራሮች አቅም በፈቀደ መጠን ለኑሮ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ የቤት ዕቃዎች ሊማሉላቸዉ ይችላል፡፡ በዚህ መሠረት ለተጠቃሚዉ የሚሰጡ ዕቃዎች ዓይነትና ብዛት ከዚህ በታች ተዘርዝሯል፡፡

ለተቋሙ የበላይ አመራሮችና በተለየ ዉል ለሚመጡ የዉጭ ሃገር ዜጋ ባለሙያዎች

ተ.ቁ	የዕቃዉ ዓይነት	ብዛት	ምርመራ
1	አልጋ	በመኝታ ቤቱ ብዛት ልክ	
2	የስፖንጅ ፍራሽ	በአልጋዉ ቁጥር	
3	የስፖንጅ ትራስ	እንደ አልጋዉ ስፋት እና ቁጥር	የአልጋዉ ስፋት 1.20 ሳ.ሜ እና በላይ ከሆነ ሁለት 0.90 ሳ.ሜ ከሆነ አንድ
4	ስቶቭ	1	
5	ሶፋ ሙሉ ሴት	1	
6	ሲሊንደር	1	
7	የምግብ ጠረጴዛ ከስድስት ወንበር ጋር	1	
8	ኮመዲና/ለማብሰያ ክፍል/	1	
9	ከመፃፊያ ጠረጴዛ ጋር የሚሄድ ወንበር	1	
10	የመፃፊያ ጠረጴዛ	1	
12	የመጽሐፍ መደርደሪያ/ሼልፍ/	1	6 መደርደርያዎች ያሉት
13	ፍሪጅ		
14	ቁምሳጥን የመኝታ ቤት		

15.2. ተጠቃሚው የማይፈልጋቸው ዕቃዎች እንደወሰዱ በተጠየቀ በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ አግባብነት ወዳለው መጋዘን በቤቶች አስተዳደር አማካኝነት እንዲመለሱ ይደረጋል፡፡

15.3. ተጠቃሚው ያለአግባብ ከአገልግሎት ውጭ ያደረጋቸውን ዕቃዎች የዋጋ ግምት ይከፍላል የዋጋ ግምት የተከፈለበት ውጭ የሆነ ዕቃ በ አንድ (1) ወር ጊዜ ይተካል፡፡

አንቀጽ 16 - የመኖሪያ ቤት ጥገና

16.1. የኢንስቲትዩቱ መኖሪያ ቤቶች ሁኔታ በየአመቱ እየታየ ተገቢውን እንክብካቤ ማግኘቱ ይረጋገጣል፣አግባብነት ያለው ጥገናም ይደረግለታል፡፡

16.2. ጥገና ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት የመኖሪያ ቤቶች ጥገና ፕሮግራሙን ቢያንስ አንድ ሳምንት በማስቀደም ለነዋሪው ያሳውቃል፡፡ ነገር ግን በሌላ ነዋሪ ላይ ችግር እያስከተለ ያለ ሁኔታ መኖሩ ሲታወቅ የጥገና ፕሮግራም መኖሩን ቢያንስ አንድ ቀን አስቀድሞ ለሚመለከተው ነዋሪ በማሳወቅ ጥገናው ይከናወናል፡፡

16.3. የመኖሪያ ቤት ጥገና ጥያቄ ከተጠቃሚው ሲቀርብ ችግሩ አፋጣኝ መፍትሄ ማግኘት ያለበት (እንደ ኤሌክትሪክ መቋረጥ እና አደጋ ወይም ከባድ የውሀ እና የፍሳሽ መስመር ሊኬጅ) ከሆነ በተቻለ ፍጥነት በዕለቱ እንዲጠገን ይደረጋል፡፡

16.4. ጥያቄው መደበኛ የጥገና ጥያቄ ከሆነ በተቋሙ የቤቶች ጥገና ክፍል አማካኝነት የሚከናወን ይሆናል፡፡ ዋና ዋና የጥገና ወጪ በተቋሙ የሚሸፈን ሲሆን የጥገና ቅደም ተከተልና የጥገና ወጪ ግምት በቅድሚያ ቀርቦ በተገቢው አካል ሲፀድቅ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

16.5. ጥቃቅን ጥገናዎች በኗሪው የሚፈፀሙ ይሆናሉ ማለትም የመብራት ተገጣጣሚዎች ብልሽት፣የውሀ መስመር ተገጣጣሚዎች ብልሽት፣የመፀዳጃ ቤትና መታጠቢያ ቤት ተገጣጣሚዎች ብልሽትን የመሣሠሉት በኗሪው የሚጠገኑ ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 17 - የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ግዴታ

17.1. ነዋሪው ቤቱን ከኢንስቲትዩቱ ሲረከብ በሚደረገው የውል ስምምነት የተሸፈነ መብትና ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው እያንዳንዱ የኢንስቲትዩቱ መኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ቤቱንና በውስጡ ያሉትን ንብረቶች በጥንቃቄ ይዞ መጠቀም አለበት፤

17.2. በተጠቃሚው አያያዝ ጉድለት ለደረሰ ማንኛውም ጉዳት ተጠቃሚው ተጠያቂ ስለሆነ በራሱ ወጪ ብልሽቱ እንዲስተካከል ያደርጋሉ፡፡

17.3. የመብራት፣ የውሀና የስልክ ወጪዎች በወቅቱ መክፈል አለበት፣ ሲያስረክብም ዕዳውን አጠናቆ ለመክፈልና በወቅቱ ላልተከፈለ ሂሳብ የሚያስፈልገውን መጠባበቂያ ክፍያ ለማስያዙ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡ በወቅቱ ባለመክፈሉ በሌላ ነዋሪ ላይ የሚደርስ ጉዳት ካለ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

17.4. ማንኛውም ተጠቃሚ ለተቋሙ ሳያሳውቅ የሚኖርበትን ቤት ከ ሁለት (2) ወራት ለበለጠ ጊዜ ተዘግቶ እንዲቆይ ማድረግ የለበትም፡፡ ይህም የሚያጋጥመው ከሆነ ለኢንስቲትዩቱ የቤቶች አስተዳደር ቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡፡የነዋሪው ፍላጎት ከሆነ መኖሪያ ቤቱን ለተቋሙ በዚህ መመሪያ ለተደነገገ ጊዜ ብቻ በጊዜያዊነት በአደራ አስረክቦ መሄድ ይችላል፤

17.5. ማንኛውም ተጠቃሚ የመኖሪያ ቤቱን መገልገል ያለበት የሌላውን መብት በማይነካ ሁኔታ መሆን አለበት፡፡ከፍተኛ ድምጽ ያለው ሙዚቃ መልቀቅ፣ሁከትና ጩኸት ሰክሮ ነዋሪዎችን መረበሽ እና የመሳሰሉት አዋኪ ተግባሮችን መፈጸም የተከለከሉ ናቸው፡፡

17.6. እንደ አስፈላጊነቱ ወቅታዊ የንብረት ቆጠራ በሚደረግበት ጊዜ ከክፍሉ በቅድሚያ በሚገለፀው ማስታወቂያ መሰረት ቤቱን ክፍት አድርጎ መጠበቅ አለበት፡፡ በወቅቱ ነዋሪው የማይኖር ከሆነ አግባብ ያለውን የቤተሰብ አባል ውስጥ እንዲገኝ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

አንቀጽ 18 - የኢንስቲትዩቱ ግዴታ

18.1. በሌሎች ውሎች የተሸፈኑ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ለመኖሪያቤት የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች ኮንትራቱን በማገናዘብና አቅም በፈቀደ መጠን በወቅቱ ያሟላል፡፡ ተጠቃሚው ከጥቃቅን ጥገና ውጭ የሆነ የመኖሪያ ቤት መገልገያ ቁሳቁስ ጥገና እንዲደረግለት ጥያቄ ሲያቀርብ ከ7 የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲጠገንለት ይደረጋል፤

18.2. ከነዋሪው አቅም በላይየሆነ የመኖሪያ ቤት ጥገና ጥያቄ ሲቀርብለት እንደስራው ስፋትና ውስብስብነት አኳያ ታይቶ በወቅቱ ምላሽ ይሰጣል፡፡

18.3. የኢንስቲትዩት ነዋሪዎች ለተወሰነ ጊዜ በአደራ እንዲጠበቅላቸው የሚሰጡትን ቤቶች ባሉበት ሁኔታ ጠብቆ መልሶ ያስረክባል፡፡

አንቀጽ 19- የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

19.1. ይህን መመሪያ በሚጥስ ሁኔታ የተያዙ ቤቶች መመሪያውን ለማስከበር በሚያስችል ሁኔታ በቤት ደልዳይ ኮሚቴ እየታዩ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡

አንቀጽ 20 - ቅሬታ አቀራረብ በተመለከተ

20.1. አንድ መምህር በመኖሪያ ቤት ድልድል /ውደድር/ ቅሬታ ካለው ድልድሉ /ውድድሩ/ ተካሄዶ በቤቶች አስተዳደር ዳይሬክተር ኃላፊ ፀድቆ የመጨረሻ ውጤት በተገለጸ በ 10 /አስር/ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በአካል በመገኘት ወይም በተወካይ ለበቤቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ማቅረብ ይችላል፡፡

20.2. የቤቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቅሬታ በቀረበለት በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስተጥ አለበት፡፡

20.3. ከላይ በቁጥር 20.2 በተገለጸው ጊዜ ምላሽ ያላገኘ መምህር ቅሬታውን ለአስተዳደር ም/ዋና ዳይሬክተር ማቅረብ ይችላል፡፡

20.4. የአስተዳደር ም/ዋና ዳይሬክተር ጉዳዩ በቀረበለት በ7 /ሰባት/ የሥራ ቀናት ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

20.5. ሂደቱን ጠብቆ የመጣ ቅሬታ የዋና ዳይሬክተሩ ምላሽ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 21 - ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

21.1. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ፡-ይህ መመሪያ በተቋሙ የሥራ አመራር ቦርድ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

21.2. ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ለተቋሙ የሥራ አመራር ቦርድ እየቀረበ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

21.3. አንድ አመልካች መምህር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በራሱ ፣ በትዳር ኢጋሩ የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት የሌለው መሆን ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ግን ይህንን በመተላለፍ የቤት ተጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ________________________
~~(ተጨማሪ ከአገልግሎት ክፍል ወይም ህግ ክፍል ጋር አስተያየት የሚጨመር ይሆናል፡፡)~~

21.4. የቤተሰብ አባልነትን ለማረጋገጥ የጋብቻ ሰርተፊኬትና ለልጆች ደግሞ የልደት ሰርተፊኬት ወይም በህጋዊ መንገድ የልጅነት መብት ያገኘ የጉዲፈቻ ልጅ ስለመሆኑ ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡